9ኛ ዓመት ቁጥር 10
9th Year No. 10

ባህር ዳር ሚያዝያ 12 ቀን 1996 ዓ/ም
Bahir Dar, 20th day of April, 2004

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State
in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 17.40
Unit price **17.40**

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 97/1996 ዓ.ም.
የአማራ ብሔራዊ ክልል ፀጥታ ምክር ቤት ማቋቋሚያና ማደራጃ አዋጅ

Content

Proclamation No. 97/2004
The Amhara National Region Security Council Establishment and Organization Proclamation

አዋጅ ቁጥር 97/1996 ዓ.ም.

የአማራ ብሔራዊ ክልል ፀጥታ ምክር ቤትን ለማቋቋምና ለማደራጀት የወጣ አዋጅ

በክልሉ ውስጥ ለሚካሔደው የኢኮኖሚያዊ ልማት እንቅስቃሴም ሆነ የዲሞክራሲያዊ ስርዓትና የመልካም አስተዳደር ግንባታ አስተማማኝ ሰላምና ዘላቂነት ያለው መረጋጋት መስፈኑ አማራጭ የማይገኝለት ጉዳይ በመሆኑ፤

የብሔራዊ ክልሉን ሰላምና ደህንነት ባልተጠበቀ ሁኔታ ከሚከሠቱም ሆነ አመጣጣቸው ሊታይ ከሚችል አደጋዎች በመጠበቅና በመከላከል ረገድ ተጨማሪ ዋስትና ሊያስገኝ የሚችል አደረጃጀት መፍጠርና አሠራር መቀየስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የነዋሪውን ህዝብ የተረጋጋ ኑሮ ለማረጋገጥና ሕግና ሥርዓትን ቀጣይነት ባለው አኳኋን ለዘለቄታው ለማስከበር ይቻል ዘንድ በየጊዜው የሚከሰቱ ፀጥታነክ ችግሮችን የክልሉ ፖሊስና የፀጥታ አጠባበቅ አካላት ከፌዴራሉ መንግስት የፀጥታ፣ የመከላከያና የደህንነት ኃይሎች ጋር የተዋሃደ ቅንጅት ፈጥረው የሚንቀሣቀሱበትን አሠራር ተቋማዊ ቅርፅና ሕጋዊ ሽፋን እንዲያገኝ ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

Proclamation No. 97/2004

A Proclamation Issued to Establish and Organize the Amhara National Region Security Council

WHEREAS, the prevalence of reliable peace and everlasting stability is a matter with no choice for economic development activity as well as the building up of democratic system and good governance undertaken in the Region;

WHEREAS, it is necessary to establish an organization enabling to have additional guaranty and to devise a mechanism with a view to safeguarding and protecting against unforeseeable and potential threats and challenges to the National Region's Security;

WHEREAS, with a view to ensuring the stable living of the inhabitants and ever maintain law and order in a sustainable manner, it is thus found appropriate causing to have organizational structure and legal coverage for the operational framework in which the Regional police as well as organs of security keeping are on action by creating integrated collaboration together with the Federal Government peace keeping, defense and security forces to deal with security related problems occurring all the time;

ይኸው ቅንጅታዊ ተቋም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ከመጣው ውስብስብ የፀጥታ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ተልዕኮ ተቀርጸለት በክልል፣ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ እርከኖች ከላይ እስከታች እንዲደራጅ ማድረግ በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it is necessary to cause that this collaborative organization to be organized at Regional, Zonal, Woreda and Kebele levels from top to bottom, with the formulation of a mission agreeable to the complex security condition growing from time to time;

የየእርከኑን አደረጃጀቶች እንደአግባቡ በክልል ርዕሰ መስተዳድርና በየደረጃው ዋና አስተዳዳሪዎች እንዲመሩ ከማድረግ ባሻገር ክልላዊው የፀጥታ ምክር ቤት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት አዋጅ ቁጥር 257/1994 ዓ.ም. መሠረት ከተቋቋመው የብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት ጋር እንዲተሣሰርና ፀጥታ ነክ ጉዳዮችን አስመልክቶ የዕቅድ፣ የሪፖርትም ሆነ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲዘረጋለት አድርጐ ማዋቀር ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, apart from causing that organizations of each level to be directed by the Head of the Regional Government and the chief administrators of each level, it is found proper that the Regional Security Council to be intertwined concerning security matters with the National Security Council, which is established in accordance with the Federal Government Proclamation No. 257/2001 and to organize it with a system designed for planning, reporting as well as for information exchange;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል::

NOW, THEREFORE, The Council of the Amhara National Region, in accordance with the powers vested in it under Article 49 Sub-Article 3/1 of the Revised Constitution of the National Region, hereby issues this proclamation.

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የአማራ ብሔራዊ ክልል ፀጥታ ምክር ቤት ማቋቋሚያና ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 97/1996 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

1. <u>Short Title</u>

This proclamation may be cited as " The Amhara National Region Security Council Establishment and Organization Proclamation No. 97/2004."

2. <u>ስለመቋቋም</u>

1. በአማራ ብሔራዊ ክልል ውስጥ ፀጥታ ነክ ተግባራትን ተቀናጅቶ የሚያቅድ፣ የሚያስተባብርና በሚወሰዱ እርምጃዎች ላይ የአማካሪነት ሚና ያለው ክልል አቀፍ ፀጥታ ምክር ቤት /ከዚህ በኋላ "ምክር ቤቱ" እየተባለ የሚጠራ አካል/ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::
2. ምክር ቤቱ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ አስተዳደሮች በተመሣሣይ የሚደራጁ ንዑሣን ምክር ቤቶች ይኖሩታል::

2. <u>Establishment</u>

1. There shall be established under this proclamation a Region-wide Security Council /herein after referred to as " The Council"/ which collaboratively plans and co-ordinates security related activities in the Amhara National Region and having an advisory role for measures to be taken thereof.
2. The Council shall have Sub councils, which shall be similarly organized at Zonal, Woreda and Kebele administrations.

3. ዓላማ

የአዋጁ ዓላማ በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ የሚያጋጥሙትንና ሊያጋጥሙ የሚችሉትን ፈርጀ ብዙ ፀጥታ ነክ ችግሮች ከተናጠል የፌዴራልና የክልሉ አስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ኃላፊነት ጋር በማይጋጭ ሁኔታ የጋራ ቅንጅት ፈጥሮ በመቆጣጠር፣ የነዋሪውን ህዝብ ዘላቂ ሰላም በመጠበቅና ደህንነቱን አስተማማኝ በማድረግ ለክልሉ ልማትና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ አስተዋጽኦ ማድረግ ነው።

4. ስለ ክልል ፀጥታ ምክር ቤት አባላት ተዋፅኦና አመራር

1. የክልል ፀጥታ ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 60 ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ ቁጥር "ቀ" ድንጋጌ መሠረት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚመራ ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱት አባላት ይኖሩታል፡-

   ሀ. የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር-------------ምክትል ሰብሣቢ
   ለ. የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ -----------------አባል
   ሐ. የክልሉ የማስታወቂያ ቢሮ ኃላፊ ---------------------- አባል
   መ. የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽነር ------- አባል
   ሠ. የክልሉ ሚሊሻ ጽ/ቤት ኃላፊ --- አባል
   ረ. የርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት ኃላፊ ---------------------አባልና ፀኃፊ
   ሰ. ርዕሰ መስተዳድሩ በክልሉ ከሚገኙ አግባብ ያላቸው የክልልና የፌዴራሉ መንግስት አካላት ተወካዮች መካከል መርጦ የሚሰይማቸው ሶስት ሰዎች --------------------------- አባላት

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ ድንጋጌ ቢኖርም ርዕሰ መስተዳድሩ ማንኛውም ሰው ሙያዊ ምክር ለመስጠት በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በአስረጅነት እንዲገኝ ለመፍቀድ ይችላል።

3. Objective

The Objective of this Proclamation is to contribute for the development of the Region and the building up of the democratic system by creating joint co-ordination and controlling over multidimensional security related problems that are occurring and have the potential to be happening in the National Region in a manner having no contrast with independent powers and responsibilities of the Federal and Regional Executive Organs, and thereby maintain the ever lasting peace of the inhabitant and make its well-being reliable.

4. Composition and Management of Members of the Regional Security Council

1. The Regional Security Council being directed by the Head of the Regional Government in accordance with Article 60 Sub-Article 3(i) of the revised Constitution of the National Region, shall have the members indicated herein under:

   A. The Deputy Head of the Regional Government ----------------Vice-chairperson
   B. The Head of Administrative and Security Affairs Bureau------------------Member
   C. The Head of Bureau of Information----------------------------Member
   D. The Regional Police Commissioner------------------------Member
   E. The Head of Office of the Militia of the Region------------------Member
   F. The Head of Office of the Head of Government -----Member & Secretary
   G. Three persons elected and designated by the Head of the Government among from those representatives of the Regional and Federal Government organs who are in the Region and having relevancy------------------------------Members

2. Notwithstanding the provision of Sub-Article 1 of this Article, the Head of the Regional Government may allow any person to attend meetings of the Council with a status of an expert adviser.

5. ስለምክር ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት

ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

1. የክልሉን ነዋሪ ህዝብ ሰላምና ደህንነት የሚመለከቱ ሀገራዊ ፖሊሲዎች ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥመው በሚገባ ተግባራዊ መደረጋቸውን በመከታተል ረገድ ርዕሰ መስተዳድሩን ያማክራል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ለክልሉ አጠቃላይ ደህንነት የስጋት ምንጭ የሆኑ ሁኔታዎችን በመገምገም ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ሃሣብ ያቀርባል፤
3. የክልሉን ደህንነት ለማስጠበቅ የሚወሰዱ እርምጃዎችን የሚመለከቱ የማስፈፀሚያ መመሪያዎችን ያመነጫል፤
4. የክልሉን ደህንነት በሚነካ በማናቸውም ጉዳይ ላይ ይመክራል፤
5. በክልሉ ውስጥ ለፀጥታ መናጋት መንስኤ የሆኑትንና ሊሆኑ የሚችሉትን ችግሮች በዝርዝር በማጥናት፣ በመገምገምና በመተንተን መፍትሄዎችን በአማራጭ ያስቀምጣል፣ ለተግባራዊነታቸውም የተቀናጀ እቅድ በማውጣት በግልፅ የስራ ክፍፍል ላይ ተመስርቶ ይንቀሣቀሣል፤
6. የክልሉን የፀጥታ ሁኔታ በሚመለከት ከብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት ጋር የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፣ ከሁሉም አካላት የሚሰበሰበውን የመረጃ ግብዓት ለፀጥታ አጠባበቅ መነሻ በማድረግ የፀጥታ ዕቅድ እያወጣ በስራ ላይ ያውላል፤
7. በክልሉ ውስጥ ያሉ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑና ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ተቋማት በቂና የተስተካከለ ጥበቃ ያላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

5. Duties and Responsibilities of the Council

The Council, pursuant to this proclamation, shall have the following duties and responsibilities:

1. Advise the Head of the Government with regard to the follow up that polices of the country relating to the peace and well-being of inhabitants of the Region are properly implemented conformable with the realities of the Region;
2. Without prejudice to the generality of sub-Article 1 of this Article, assess threats of entire security of the Region and forward recommendations on measures to be taken thereof;
3. Generate execution directives concerning measures to be taken for safeguarding security of the Region;
4. Deliberate on any issue affecting security of the Region;
5. Put forward alternative recommendations by studying in detail, evaluating and analyzing problems which are the cause and potential threats of insecurity in the Region, and be on action by designing integrated plan and depending on transparent division of work for the implementation of same;
6. Make information exchange with the National Security Council relating to security of the Region; set out security plan and thereby implement same by making the information input gathered from all bodies as a spring board for security safety;
7. Ensure that institutions in the Region which are vulnerable to danger and those necessitate safeguarding have sufficient and arranged keeping;

8. የህዝቡን የፀጥታ ስነ-አዕምሮ ለማዳበር የሚያስፈልጉ ስራዎችን ያከናውናል፣ በሆቴሎችና በግል ተቋማት የተቀጠሩ የጥበቃ ሰራተኞች የሚሰለጥኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ከፖሊስና ሌሎች የፀጥታ ሀይሎች ጋር ግንኙነቶችን በመፍጠርና የሪፖርት ልውውጥ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ በተቻለ መጠን አንድ ወጥ ፀጥታ ነክ የእቅድ ቅንጅትና የመረጃ አጠቃቀም ስርዓት እንዲኖር በሚደረገው ጥረት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል፤

9. ክልሉን አቋርጠው የሚያልፉ ዋና ዋና መንገዶች በታጠቁም ሆነ ባልታጠቁ ዘራፊዎች እንቅስቃሴን የሚያውክ ተግባር እንዳይፈፀም የፀጥታ ሀይሉን ከገጠሩ የሚሊሻ ሀይል ጋር አጣምሮ የተሟላ ጥበቃ ያላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

10. በክልሉ ውስጥ ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ንግድ እንዳይካሄድና የትጥቅ ዝውውር እንዳይፈፀም ይከታተላል፣ ድርጊቱን ፈጽመው በተገኙት ላይም ተገቢው ሕጋዊ ርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

11. በክልሉ ውስጥም ሆነ ካጐራባች ክልሎች ጋር በሚያዋስኑ ይዞታዎች ሊያጋጥሙ የሚችሉ ግጭቶችን አስቀድሞ በማጥናትና በጥንቃቄ በመያዝ የሚወገዱበትን መፍትሄ ያፈላልጋል፣ ክልል አቀፍ የግጭት መከላከልና አፈታት ስትራቴጂ ያወጣል፣ ከአጐራባች ክልሎች አቻ አደረጃጀቶች ጋር ተግባብቶና ተቀናጅቶ ይንቀሣቀሣል፤

12. ፈፃሚ አካላት በግጭት መከላከልና በሠላም ግንባታ ረገድ ያላቸው ግንዛቤ በየጊዜው እንዲዳብር ይሠራል፤

13. ፀጥታን በሚመለከት በቅንጅት የወጣው እቅድ በስራ ክፍፍል ላይ ተመስርቶ በተናጠል አካላቱ እንዲፈፀም ውሣኔዎችን ያሣልፋል፤

8. Carry out activities necessary for the development of mental tranquility of the inhabitants; facilitate the condition for training guards employed in hotels and private institutions; follow up the implementation of same by making relation with police and other security forces and by putting in place report exchange system; make its own contribution, to the extent possible, in an effort being exerted to have uniform security related plan co-ordination and information utilization system;

9. Ensure that there is complete guarding by integrating the security force with the country-side militia force in order that an act of obstructing movements not to be committed by armed or non-armed robbers over the main roads crossing through the Region;

10. Follow up that illegal arms trading and arms trafficking not be committed in the Region, and cause an appropriate legal measure to be taken against those who are found committing the act;

11. Search a solution for the avoidance of clashes that may happen in the Region as well as in possessions bordering with the neighboring Regions through studying them in prior and keeping same in safe; set out a strategy of Region-wide conflict protection and resolution; be on action in harmony and integration with the corresponding organizational structures of the neighboring Regions;

12. Work regularly to promote the awareness of the operating bodies relating to conflict protection and promoting peace;

13. Make decisions that the plan set out on collaboration concerning security be executed by its independent bodies based on the division of work;

14. ፀጥታን በሚመለከት ከክልሉ አቅም በላይ የሆነ ምክንያት ተፈጥሮ ሲገኝ ከብሔራዊው የደህንነት ምክር ቤት ጋር አስፈላጊውን ቅንጅት ያደርጋል፣ ለዚህም እንዲያመች በየጊዜው ስለክልሉ ፀጥታ ነክ እንቅስቃሴዎች ለሀገራዊው የደህንነት ምክር ቤት ያሣውቃል፣

15. በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 114 ንዑስ አንቀጽ 1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሲደነግግ አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦች ተወስነው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

6. ስለምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የውሣኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት

1. ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባውን በወር አንድ ጊዜ ያካሂዳል::
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ በርዕሰ መስተዳድሩ ሲጠራ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል::
3. በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል::
4. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ ሆኖም ድምፁ እኩል በተከፈለ ጊዜ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል::
5. ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ስነ-ስርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል::

7. ምክር ቤቱ ራሱን በኮሚቴዎች ስለሚያደራጅበት ሁኔታ

1. ምክር ቤቱ ለስራው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ራሱን በልዩ ልዩ ኮሚቴዎች አደራጅቶ ሊንቀሣቀስ ይችላል፣

14. Make the necessary collaboration with the National Security Council whenever a reason concerning security to be found happened beyond the capacity of the Region; and to be conducive thereto, inform regularly security related activities of the Region to the National Security Council;

15. Carry out other duties specifically entrusted to it by regulations to be issued for the implementation of the declaration where the Council of the Regional Government decrees state of emergency in accordance with the power vested in it under Article 114 Sub-Article 1 of the Revised Constitution of the National Region.

6. Meeting Schedule and Decision Making Procedures of the Council

1. The Council shall hold its ordinary meeting once a month.
2. Without prejudice to the provision of sub-Article 1 of this Article, the Council may have meetings at any time whenever convened by the Head of the Government.
3. The presence of more than half members shall constitute quorum for any meeting of the Council.
4. Decisions of the Council shall be passed by a majority vote and; incase of a tie, the chairperson shall have a casting vote.
5. The Council may adopt its own rules of procedure.

7. Condition for Organizing the Council into Committees

1. The Council may organize itself in various committees and thereby be on action when it deems necessary for its performance;

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ የሚቋቋሙት ኮሚቴዎች አይነት፣ የአባላቱ ጥንቅርና ዝርዝር ተግባራቸው በምክር ቤቱ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

8. ስለምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት

ለዚህ አዋጅ አላማ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት የብሔራዊ ክልሉ ፀጥታ ምክር ቤት ጽ/ቤት ሆኖ ያገለግላል፡፡

9. ስለዞን ፀጥታ ምክር ቤት አባላት ተዋፅኦና አመራር

1. የዞን ፀጥታ ምክር ቤት በሚመለከተው ዞን ዋና አስተዳዳሪ የሚመራ ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱት አባላት ይኖሩታል፡-

   ሀ. የዞኑ ምክትል አስተዳዳሪ ---------------------------ምክትል ሰብሳቢ
   ለ. የዞኑ አስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ተወካይ ------------------ አባል
   ሐ. የዞን ማስታወቂያ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ ------------------------አባል
   መ. የዞን ፖሊስ ጽ/ቤት ኃላፊ-------------አባል
   ሠ. የዞን አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ ------------------------------አባልና ፀኃፊ
   ረ. የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ በዞኑ ከሚገኙት አግባብ ያላቸው የክልሉና የፌዴራሉ መንግስት አካላት ተወካዮች መካከል መርጦ የሚሰይማቸው ሶስት ሰዎች ----------------------------አባላት

2. የዞን ፀጥታ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለክልል ፀጥታ ምክር ቤት ይሆናል፡፡

10. ስለዞን ፀጥታ ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት

የዞን ፀጥታ ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

2. The type, composition of members and detailed duties of those committees to be established when the provisions of Sub-Article 1 of this Article coming into effect shall be determined by a directive the Council issues thereon.

8. Office of the Council

Office of the Head of the Regional Government, for the objective of this proclamation, shall serve as the Office of the National Region Security Council.

9. Composition and Management of Zonal Security Council

1. Zonal Security Council being directed by the concerned Zonal Chief Administrator shall have the members indicated herein under:

   A. The Deputy Administrator of the Zone --------------------Vice chairperson
   B. Representative of the Zone Administrative and Security Affairs Coordinating Office-----Member
   C. Head of the Zone Information Branch Office--------------------Member
   D. Head of the Zone Police Office--Member
   E. Head of the Zone Administration Office------------- Member and Secretary.
   F. Three persons elected and designated by the Chief Administrator of the Zone among from representatives of Regional and Federal Government Organs who are in the Zone and having relevancy------------------------------Members

2. The Zonal Security Council shall be accountable to the Regional Security Council.

10. Duties and Responsibilities of Zonal Security Council

Zonal Security Council shall have the duties and responsibilities indicated herein under:

1. የዞኑን ነዋሪ ህዝብ ሰላምና ደህንነት የሚመለከቱ ሀገራዊና ክልል አቀፍ ፖሊሲዎችና የማስፈፀሚያ መመሪያዎች ከዞኑ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥመው በሚገባ ተግባራዊ መደረጋቸውን በመከታተል ረገድ ዋና አስተዳዳሪውን ያማክራል፤

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ለዞኑ አጠቃላይ ደህንነት የስጋት ምንጭ የሆኑ ሁኔታዎችን በመገምገም ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ሀሣብ ያቀርባል፤

3. የዞኑን ደህንነት ለማስጠበቅ የሚወሰዱ እርምጃዎችን አስመልክቶ ከክልሉ ፀጥታ ምክር ቤት እንዳስፈላጊነቱ የሚተላለፉ መመሪያዎችን ተቀብሎ ያስፈፅማል፤

4. የዞኑን ደህንነት በሚነካ በማናቸውም ጉዳይ ላይ ይመክራል፤

5. በዞኑ ውስጥ ለፀጥታ መናጋት መንስኤ የሆኑትንና ሊሆኑ የሚችሉትን ችግሮች በዝርዝር በማጥናት፣ በመገምገምና በመተንተን መፍትሔዎችን በአማራጭ ያስቀምጣል፣ ለተግባራዊነታቸውም የተቀናጀ እቅድ በማውጣት በግልፅ የስራ ክፍፍል ላይ ተመስርቶ ይንቀሣቀሣል፤

6. የዞኑን የፀጥታ ሁኔታ በሚመለከት ለክልሉ ፀጥታ ምክር ቤት ወቅታዊ የስራ ሪፖርት ያቀርባል፣ ከሁሉም አካላት የሚሰበሰበውን የመረጃ ግብዓት ለፀጥታ አጠባበቅ መነሻ በማድረግ የፀጥታ ዕቅድ እያወጣ በስራ ላይ ያውላል፤

7. በዞኑ ውስጥ ያሉ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑና ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ተቋማት በቂና የተስተካከለ ጥበቃ ያላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

8. በዞኑ የሚያልፉ ዋና ዋና መንገዶችና የመሠረተ ልማት አውታሮች በታጠቁም ሆነ ባልታጠቁ ዘራፊዎች እንቅስቃሴን የሚያውክ ተግባር እንዳይፈፀም የፀጥታ ኃይሉን ከገጠሩ የሚሊሻ ኃይል ጋር አጣምሮ በማሰማራት የተሟላ ጥበቃ ያላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

1. Advise the Chief Administrator with regard to the follow up that National and Region-wide polices and execution directives relating to the peace and well-being of inhabitants of the zone are properly implemented conformable with the realities of the zone;

2. Without prejudice to the generality of sub-Article 1 of this Article, assess threats of entire security of the Zone and forward recommendations on measures to be taken thereof;

3. Receive and enforce guidelines dispatched from the Regional Security Council, as deemed necessary, concerning measures to be taken to maintain the security of the zone,

4. Deliberate on any issue affecting security of the Zone;

5. Put forward alternative recommendations by studying in detail, evaluating and analyzing problems which are the cause and potential threats of insecurity in the Zone, and be on action by designing integrated plan and depending on transparent division of work for the implementation of same;

6. Submit periodic performance report to the Regional Security Council regarding the security of the zone; set out security plan and thereby implement same by making the information input gathered from all bodies as a spring board for security safety;

7. Ensure that institutions in the zone which are vulnerable to danger and those necessitate safeguarding have sufficient and arranged guarding;

8. Ensure that there is complete guarding by integrating the security force with the country-side militia force in order that an act of obstructing movements not to be committed by armed or non-armed robbers over main roads and infrastructure crossing the zone;

9. በዞኑ ውስጥ ሕገ-ወጥ ንግድንና የትጥቅ ዝውውርን ይከታተላል፣ በተገኘ ጊዜም ጉዳዩ ለሕግ እንዲቀርብ ያደርጋል፤

10. በዞኑ ውስጥ የፀጥታ አጠባበቅ ስራዎችን ያስተባብራል፣ ማናቸውም የፀጥታ መደፍረስ ሁኔታ ሲያጋጥም ለበላዩ መረጃ ሰጥቶ አፋጣኝ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፣ ችግሩ ከዞኑ አቅም በላይ መሆኑን ሲረዳው የክልሉን ፀጥታ ምክር ቤት ድጋፍ ይጠይቃል::

11. የስብሰባ ጊዜና የውሣኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት

1. የዞን ፀጥታ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን በሃያ ቀን አንድ ጊዜ ያካሂዳል::
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ከንዑስ አንቀጽ 2 እስከ ንዑስ አንቀጽ 5 የሠፈሩት ድንጋጌዎች አግባብነታቸው እየታየ ለዞን ፀጥታ ምክር ቤትም በተመሣሣይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል::

12. ስለምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት

የዞን አስተዳደር ጽ/ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት የዞን ፀጥታ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ጭምር ሆኖ ያገለግላል::

13. ስለወረዳ ፀጥታ ምክር ቤት አባላት ተዋፅኦና አመራር

1. የወረዳ ፀጥታ ምክር ቤት በሚመለከተው ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ የሚመራ ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱት አባላት ይኖሩታል:-
   - ሀ. የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ ----------------------------ምክትል ሰብሣቢ
   - ለ. የወረዳ አስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ-------------------አባል
   - ሐ. የወረዳ ማስታወቂያ ጽ/ቤት ኃላፊ ------------------------------አባል
   - መ. የወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት ኃላፊ-----------አባል
   - ሠ. የወረዳ ሚሊሻ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ ---------------------------አባል
   - ሰ. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ በወረዳው ውስጥ ከሚገኙ አግባብ ያላቸው የክልሉና የፌዴራሉ መንግስት አካላት ተወካዮች መካከል መርጦ የሚሰይማቸው ሶስት ሠዎች --------አባላት
   - ረ. የወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ ---------------------------- አባልና ፀኃፊ

9. Follow up illegal trading and arms trafficking, and cause the issue of same appear before the law when found committed;

10. Co-ordinate security maintaining activities in the zone; inform to its superior and cause immediate measures to be taken when any insecurity occurs; and request the support of the Regional Security Council when it realizes that the problem is beyond the capacity of the Zone.

11. Meeting Schedule and Decision Making Procedure

1. The Zonal Security Council shall hold its regular meeting once in twenty days.
2. The provisions provided from Sub-Article 2 to Sub-Article 5 of Article 6 of this proclamation shall, mutatis mutandis, apply to the Zonal Security Council.

12. Office of the Council

Office of the Zonal Administration shall also be the Office of the Zonal Security Council pursuant to this proclamation.

13. Composition and Management of Members of the Woreda Security Council

1. The Woreda Security Council being directed by the concerned Woreda Chief Administrator shall have the members indicated herein under:
   - A. Deputy Administrator of the Woreda ---------------------------Vice chairperson
   - B. Head of the Woreda Administrative and Security Affairs Office---------------------Member
   - C. Head of the Woreda Information Office------------------------------------Member
   - D. Head of the Woreda Police Office---- Member
   - E. Head of the Woreda Coordinating Office of the Militia ------------------- Member
   - F. Three persons elected and designated by the Chief of the Woreda among from representatives of Regional and Federal Government Organs who are in the Woreda and having relevancy --------Members
   - G. Head of the Woreda Administration Office ------------------------------ Secretary and Member.

2. የወረዳ ፀጥታ ምክር ቤት ለዚሁ አዋጅ አላማና ተፈፃሚነት ተጠሪነቱ ለሚመለከተው ዞን ፀጥታ ምክር ቤት ይሆናል::

14. ስለወረዳ ፀጥታ ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት

የወረዳ ፀጥታ ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

1. በወረዳው ውስጥ የሚያጋጥሙና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ፀጥታ ነክ ችግሮችን በዝርዝር በማጥናት አስቀድሞ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤
2. የወረዳውን ሰላምና ደህንነት በሚመለከት ከዞን ፀጥታ ምክር ቤት ጋር የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፤ መረጃውንም ለወረዳው የደህንነት ጥበቃ መነሻ በማድረግ ይጠቀምበታል፤
3. በወረዳው ውስጥ በአዲስ መልክ የሚፈጠሩ ሰብአዊና ያልተለመዱ እንቅስቃሴዎችን በንቃት ለመከታተልና ለመረዳት የሚያስችል የአሰራር ስልት ይቀይሳል፤ በስሩ በሚገኙ የቀበሌ አመራሮች፣ የሚሊሻ አባላትና በሰፊ የነዋሪው ህዝብ ተሣትፎ በመጠቀም የፀጥታ ችግሮችን አስቀድሞ ይከላከላል፤
4. የህዝቡን፣ የቀበሌ አስተዳደርና የሚሊሻ አባላትን የፀጥታ ስነ-አዕምሮ ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎችን አቅዶ ይሰራል፤
5. በወረዳው ውስጥ ያሉ የሆቴል አገልግሎት ሰጭ ተቋማት በየዕለቱ ያሣደሩትን እንግዳ መዝግበው መያዛቸውንና ለአቅራቢያው ፖሊስ ሪፖርት ማድረጋቸውን ይከታተላል፤ ቀበሌዎችና የግል ተቋማት የጥበቃ ሀይሎች ከፖሊስ ጋር በቅርብ ትስስር መፍጠራቸውን ያረጋግጣል፤

2. The Woreda Security Council shall be accountable to the concerned Zonal Security Council for the objective and implementation of this Proclamation.

14. Duties and Responsibilities of the Woreda Security Council

The Woreda Security Council shall have the duties and responsibilities indicated herein under:

1. Take corrective measures right ahead by studying in detail existing and potential security related problems in the Woreda;
2. Make information exchange with the zonal security council regarding peace and security of the Woreda, and use the information as a spring board for maintaining the security of the Woreda;
3. Devise a working procedure enabling to attentively follow up and comprehend human and unusual trends which appear in a new form in the Woreda; Protect in advance security problems by making use of the participation of Heads of the Kebele as well as members of the militia found under it and of the broad inhabitants;
4. Plan and thereby perform activities enabling to promote mental tranquility of the people, and members of the Kebele administration and of the militia;
5. Follow up establishments that provide hotel service in the Woreda keep a record of guests who daily accommodate and report same to the proximate police station, ensure that guarding forces of the Kebeles and private institutions to have created close ties with police;

6. ነዋሪውን ህዝብና ህጋዊ ታጣቂ ሀይሎችን በማስተባበር በወረዳው የሚያልፉ ዋና ዋና መንገዶች፣ ድልድዮችና የኤሌክትሪክም ሆነ የስልክ ተሸካሚ ምሰሶዎች ከማንኛውም አደጋ የተጠበቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

7. ሕገ-ወጥ ንግድንና የትጥቅ ዝውውርን ይከታተላል፤ ሲደረስበትም ጉዳዩን ለሕግ ያቀርባል፤

8. በወረዳው ውስጥም ሆነ በአዋሳኝ ይዞታዎች ለጊዜያዊ ግጭት መነሻ የሆኑ ችግሮችን አስቀድሞ ያጠናል፤ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤ ተከስቶ ሲገኝም ለግጭቱ መንስኤ የሆኑትን ለህግ በማቅረብ ሰላምን ያስጠብቃል፤

9. በፀጥታ አጠባበቅ ዕቅዱ መሠረት በሚደረገው የስራ ክፍፍል የተፈፀሙ ስራዎችን ይገመግማል፣ ውሣኔ ይሰጣል፤

10. ስለወረዳው ፀጥታ ነክ እንቅስቃሴዎች በየጊዜው ለዞኑ ፀጥታ ምክር ቤት ዘገባ ያቀርባል፣ የፀጥታ አጠባበቅ ስራዎችን ያስተባብራል፣ ማናቸውም የፀጥታ መደፍረስ ሁኔታ ሲያጋጥም ለበላዩ መረጃ ሰጥቶ አፋጣኝ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፣ ችግሩ ከወረዳው አቅም በላይ መሆኑን ሲረዳው የዞኑን ፀጥታ ምክር ቤት ድጋፍ ይጠይቃል፡፡

15. ስለስብሰባ ጊዜና የውሣኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት

1. የወረዳ ፀጥታ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን በአስራ አምስት ቀን አንድ ጊዜ ያካሂዳል፡፡

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ከንዑስ አንቀጽ 2 እስከ ንዑስ አንቀጽ 5 የሰፈሩት ድንጋጌዎች አግባብነታቸው እየታየ ለወረዳ ፀጥታ ምክር ቤትም በተመሣሣይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

6. Ensure, by coordinating the inhabitants and legal armed forces, that main roads crossing through the Woreda, bridges, and electric as well as telecommunication towers are protected from any danger;

7. Follow up illegal trading and arms trafficking, and where same found committed take the case before the law;

8. Study in prior problems which are causes for temporary clashes in the Woreda as well as on bordering possessions, take corrective measures thereto, and cause the maintenance of peace by bringing the perpetrators before the law when same found occurred;

9. Evaluate and thereby make decision on the activities performed on division of work pursuant to the plan of security keeping;

10. Submit a report regularly to the Zonal Security Council on security related activities; coordinate security maintaining activities; inform to its superior and cause immediate measures to be taken when any insecurity occur; and request the support of the Zonal Security Council when it realizes that the problem is beyond the capacity of the Woreda.

15. Meeting Schedule and Decision Making Procedure

1. The Woreda Security Council shall hold its regular meeting once in fifteen days.

2. The provisions provided from Sub-Article 2 to Sub-Article 5 of Article 6 of this proclamation shall, mutatis mutantdis, apply to the Woreda Security Council.

16. ስለምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት

የወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት የወረዳ ፀጥታ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ጭምር ሆኖ ያገለግላል፡፡

17. በከተማ አስተዳደሮች ስለሚቋቋም የፀጥታ ምክር ቤት

በከተማ አስተዳደሮች የሚቋቋመው የፀጥታ ምክር ቤት አደረጃጀት፣ ተጠሪነት፣ ተግባርና ኃላፊነት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

18. ስለቀበሌ ፀጥታ ምበር ቤት አባላት ተዋጽኦና አመራር

1. የቀበሌ ፀጥታ ምክር ቤት በሚመለከተው ቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ የሚመራ ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱት አባላት ይኖሩታል፡-

   ሀ. የቀበሌው ምክትል አስተዳዳሪ ---------------------------ምክትል ሰብሣቢ
   ለ. የቀበሌውን ሰላም ለማረጋገጥ የተመደበ የሚመለከተው ወረዳ ወይም ንዑስ ወረዳ ፖሊስ ተወካይ ------------------------------ አባል
   ሐ. የቀበሌው አስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ተጠሪ ----------------------------አባል
   መ. የቀበሌው ሚሊሻ ሀይል ተጠሪ ---------------------------------አባል
   ሠ. የቀበሌው ማስታወቂያ ጽ/ቤት ኃላፊ ------------------------አባልና ፀኃፊ
   ረ. የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ በቀበሌው ውስጥ ከሚገኙት የክልልና የፌዴራል መንግስት አካላትና ተቋማት ተጠሪዎች መካከል መርጦ የሚሰይማቸው ሁለት ሰዎች -----------------------አባላት

2. የቀበሌ ፀጥታ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለታቀፈበት ወረዳ ፀጥታ ምክር ቤት ነው፡፡

16. Office of the Council

The Office of the Woreda Administration shall also be the Office of the Woreda Security Council pursuant to this proclamation.

17. Security Council Established in City Administrations

The organization, accountability, duty and responsibility of the security council to be established in city Administrations shall be determined by a regulation that the Council of the Regional Government issues subsequent to this proclamation.

18. Composition and Management of Members of the Keble Security Council

1. The Kebele Security Council being directed by the concerned Kebele Chief Administrator shall have the members indicated herein under:

   A. The Vice Administrator of the Kebele -------------------------Vice chairperson
   B. Representative of the concerned Woreda or Sub-Woreda police assigned to ensure the peace of the Kebele --------------------------------Member
   C. The Head of Administrative and Security Affairs of the Kebele -------Member
   D. The Head of the Kebele Militia Force -----------------------------------Member
   E. The Head of the Kebele Information Office---------------------Member & Secretary
   F. Two persons elected and assigned by the Chief Administrator of the Kebele from among representatives of Regional and Federal Government organs and institutions that are in the Kebbele---------------------- Members

2. The Kebele Security Council shall be accountable to the Embracing Woreda Security Council.

19. ስለቀበሌ ፀጥታ ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት

የቀበሌ ፀጥታ ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. በቀበሌው ውስጥ ለፀጥታ መደፍረስ መንስኤ የሆኑትን ችግሮች ያጠናል፣ የመከላከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤
2. የቀበሌውን ፀጥታ በሚመለከት ከወረዳው ፀጥታ ምክር ቤት ጋር የማያቋርጥ የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፣ በሚሰጠው መመሪያ መሰረትም የቀበሌው ሰላም በዘላቂነት የተጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤
3. ለወረዳው ፖሊስ እንቅስቃሴ ተገቢው መረጃ ተደራጅቶ በወቅቱ እንዲደርሰው ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል፣ በሰላምና ደህንነት ጥበቃ ረገድ የነዋሪውን ህዝብ ንቁ ተሣታፊነት ያሣድጋል፤
4. በቀበሌው ውስጥ የመሠረተ ልማት አውታሮች ማለትም መንገዶች፣ ድልድዮች እንዲሁም የስልክና የኤሌክትሪክ መስመሮች በነዋሪው ህዝብና ህጋዊ ታጣቂ ሀይሎች አስተማማኝ ጥበቃ ማግኘታቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤
5. ሕገ-ወጥ የትጥቅ ዝውውርና የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴን በመቆጣጠር ረገድ የሚጠበቅበትን ሁሉ ለፖሊስ ያበረክታል፤
6. በጋራ የፀጥታ እቅዱ መሠረት የስራ ክፍፍል ስርዓት ዘርግቶ ይንቀሣቀሣል፣ የተፈፀሙ ስራዎችን ይገመግማል፤
7. ስለቀበሌው ፀጥታ ነክ እንቅስቃሴዎች በየጊዜው ለወረዳ ፀጥታ ምክር ቤት ዘገባ ያቀርባል፣ የፀጥታ አጠባበቅ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ማናቸውም የፀጥታ መደፍረስ ሲያጋጥም ለበላዩ መረጃ ሰጥቶ አፋጣኝ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፣ ችግሩ ከቀበሌው አቅም በላይ መሆኑን ሲረዳው የወረዳውን ፀጥታ ምክር ቤት ድጋፍ ይጠይቃል።

19. Duties and Responsibilities of the Kebele Security Council

The Kebele Security Council shall have the duties and responsibilities indicated herein under:

1. Study and thereby take protective measures on problems that are the cause for insecurity in the Kebele;
2. Make continuous information exchange with the Woreda Security Council concerning the security of the Kebele, and ensure that the peace of the Kebele is kept durable in accordance with guidelines rendered to it;
3. Make a continual effort that appropriate information is organized and periodically attain for the activity of the Woreda police, promote the active participation of the inhabitants with regard to maintaining peace and security;
4. Supervise and ensure that infrastructures in the Kebele such as roads, bridges as well as telecommunication and electric lines to have got reliable safeguarding by the inhabitants and legal armed forces;
5. Contribute what so ever expected from it to the police with regard to controlling illegal arms trafficking and contraband activities;
6. Be on action by devising a system of work division based on the joint security plan, and evaluate the activities performed thereof;
7. Submit a report regularly to the Woreda Security Council regarding security related activities of the Kebele; coordinate security maintaining activities; cause immediate measures to be taken by providing information to its superior when any insecurity occurs; and request the support of the Woreda Security Council when it realizes that the problem is beyond the capacity of the kebele.

20. ስለስብሰባ ጊዜና የውሣኔ አሠጣጥ ስነ-ሥርዓት

1. የቀበሌ ፀጥታ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን በሣምንት አንድ ጊዜ ያካሂዳል።
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ከንዑስ አንቀጽ 2 እስከ ንዑስ አንቀጽ 5 የሰፈሩት ድንጋጌዎች አግባብነታቸው እየታየ ለቀበሌ ፀጥታ ምክር ቤትም በተመሣሣይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

20. Meeting Schedule and Decision Making Procedure

1. The Kebele Security Council shall hold its regular meeting once a week.
2. The provisions provided from Sub-Article 2 to Sub-Article 5 of Article 6 of this proclamation shall, mutantis mutandis, apply to the Kebele Security Council.

21. ስለምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት

የቀበሌ አስተዳደር ጽህፈት ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት የቀበሌ ፀጥታ ምክር ቤት ጽህፈት ቤትም ጭምር ሆኖ ያገለግላል።

21. Office of the Council

The Office of the Kebele Administration shall, pursuant to this Proclamation, also be the office of the Kebele Security Council.

22. ስለጐንዮሽ ግንኙነቶች

የየደረጃው የፀጥታ ምክር ቤት አባላት ከዚህ በላይ እንደተመለከተው እርስ በርስ ያላቸው ወጥ የሥራ ግንኙነት እንደተጠበቀ ሆኖ ግጭትና ፀጥታ ነክ ጉዳዩችን አስመልክቶ በአጎራባች አካባቢዎች ከሚገኙ አቻዎቻቸው ጋር ተባብሮ የመሥራት ግዴታ አለባቸው።

22. Horizontal Relations

Without limiting to each other's uniform work relation, as indicated above, members of the security council of each level are duty bound to work collaboratively with their corresponding found in neighboring localities concerning conflict and security related affairs.

23. የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጐች

1. የአማራ ብሔራዊ ክልል ፀጥታ ምክር ቤትና የተዋረድ አካላቱን አደረጃጀት፣ ኃላፊነትና አሠራር ለመወሰን የወጣው የክልል መስተዳድር ምክር ቤት መመሪያ ቁጥር 4/1995 ዓ.ም. በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

23. Repealed and Inapplicable Laws

1. The Regional Government Council Directive No. 4/2003 issued to determine the Organization, Responsibility and Operation of the Amhara National Region Security Council and its hierarchical bodies shall be repealed by this proclamation.
2. Any proclamation, regulation, directive or customary practice inconsistent with this proclamation shall not be applicable on matters provided in this proclamation.

24. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያገለግለውን ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

24. Power to Issue Regulation and Directive

1. The Council of the Regional Government may issue a regulation necessary for the full implementation of this proclamation.

2. የክልሉ ርዕሰ-መስተዳድር ይህንን አዋጅና አዋጁን ተከትሎ ለሚወጣው ደንብ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

25. አዋጁ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህርዳር
ሚያዝያ 12 ቀን 1996 ዓ.ም.

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

2. The Head of the Government may issue detailed directives necessary for the implementation of this proclamation and regulation to be issued subsequent to this proclamation.

25. Effective Date

This Proclamation shall come into force commencing the day of its publication in the ***Zikere Hig Gazetta*** of the Region.

Done at Bahir Dar
This 20th day of April, 2004

Yosef Retta
President of the Amhara National Region